Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# አካታች እና ምቹ ትምህርት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)



ለተከበራችሁ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበረሰብ፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አካታች እና ምቹ የመማሪያ አካባቢን ለማዳበር ቁርጠኛ ስለሆነ፥ ሁሉም ተማሪዎች እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን በስርአተ ትምህርት ቁሳቁሶች ላይ የሚያዩበትን እድል ለመፍጠር ይፈልጋል።

ከትምህርት ቦርድ መርሕ/ፖሊሲ ጋር በማጣጣም፣ MCPS የወንዶች እና የሴቶችን፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎት፣ ጉዳዮችን እና ስኬቶችን በመዳሰስ ከተለያየ ዘር፣ ጎሳ፣ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ ዳራዎች እንዲሁም የተለያየ የፆታ ማንነት፣ የፆታ መገለጫ እና የፆታ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች የአካባቢ እና የአለም ማህበረሰብን ብዝሃነትና ልዩነት የሚያንፀባርቁ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን የማካተት ሃላፊነት አለበት።

ተማሪዎቻችን ከ MCPS ለኮሌጅ፣ ለስራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት ዝግጁ ሆነው እንዲወጡ ከወላጆች፣ ከተንከባካቢዎች፣ የማህበረሰብ አባላት እና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለንን አጋርነት እናከብራለን።

**MCPS ሁሉንም የሜሪላንድ እና የፌደራል የትምህርት መምሪያ ህጎችን ይከተላል፤ ስለሆነም በሁሉም ክፍሎች ላሉ ተማሪዎች ተጨማሪ የስርአተ ትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን በሚመርጥበት ጊዜ ከትምህርት ስርአቱ ዋና እሴቶች ጋር የሚጣጣም ሂደት ይከተላል።** ስለ LGBTQ+ ሁሉን አቀፍ መጽሐፍት በክፍል ደረጃ ማስተማሪያ እዚህ የቀረበውን መረጃ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲያነቡት እናበረታታለን።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

## ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች

**ቁሳቁሶች እንዴት እንደሚመረጡ፡-**

ስርዓተ ትምህርቱን የሚደግፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በተገለጹት ሂደቶች መሰረት የወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት ግምገማ እና ክለሣ የተደረገባቸው የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ባለሙያ ሰራተኞች ገምግመው ይመርጣሉ።

የዚህ አይነት አሠራር የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ምርጫ ያበረታታል፡

- ለእድሜ እና ለእድገት ደረጃ ተስማሚ የሆኑ፣
- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ትምህርት ቤቶች እንዲያስተምሩ የሚያበረታታውን የቋንቋ ስነጥበብ፣ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት ብቃት ደረጃ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ፣
- ለ MCPS ፕሮግራም አወንታዊ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ እና ከ MCPS ስርአተ ትምህርት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው።

ስለ ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡-

ደንብ IIB-RA

እና

መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት የሰፈነበት የ MCPS መርህ/ፖሊሲ

## LGBTQ+ የትምህርት መጽሑፎች እና ሪሶርሶችን ማካተት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነትን የሚያንፀባርቁ ተጨማሪ የማስተማሪያ ጽሑፎች፡- ስለ ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ባይሴክሹዋል፣ ትራንስጀንደር፣ ክዌር እና ጠያቂ ማህበረሰብ የመሳሰሉትን የሚወክሉ የማስተማሪያ ቁሳቁኦች ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (PreK-12) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ እንዲሆን ፀድቋል፣ ምክንያቱም፡-

- አካታች መጽሃፍቶች የተማሪዎችን የመረዳዳት፣ የመገናኘት እና ከተለያዩ እኩዮቻቸው ጋር የመተባበር ችሎታን ይደግፋሉ፣ እና ለሁሉም ሰው አክብሮት መስጠትን ያበረታታሉ።
- የበለጠ ታጋሽ፣ አካታች እና ተቀባይነት ያለው የትምህርት ቤት አካባቢ ልጆች የተዛባ አመለካከቶችን እንዲያውቁ እና እንዲቋቋሙ ይረዳቸዋል። ልጆች ስለሌሎች እንዲቆሙ፣ ጉልበተኝነትን እንዲቋቋሙ እና አብረው እንዲሠሩ እናስተምራለን።
- ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ ልዩነታቸው ምንም ይሁን ምን አብሮ መሥራትን እና እርስ በርስ መከባበርን ይማራሉ። የስርዓተ-ፆታ ልዩነት እና የማንነት ብዝሃነትን ግንዛቤ መፍጠር የዚህ ስራ አካል ነው።
- ስለ LGBTQ+አካታች መጽሃፍት ተቀባይነትን እና መከባበርን በማስተዋወቅ እና በአለም ላይ ስላሉ የተለያዩ ሰዎች እና ቤተሰቦች በማስተማር ሁሉንም ተማሪዎች ይጠቅማሉ።

ዓላማው፡- ስለተለያዩ ጾታዎች እና የሥርዓተ-ፆታ ማንነት በመማር ግንዛቤ ለመያዝ እንጂ ሌላ የተለየ ነገር ማስተማር አይደለም። የMCPS ቤተሰቦች ስብጥር ለወላጆች መጪ ንባቦችን፣ ውይይቶችን ወይም የክፍል እንቅስቃሴዎችን ከግል እምነታቸው ጋር ሊጋጩ የሚችሉ ነገሮችን ለማሳወቅ የማይቻል ያደርገዋል። የሜሪላንድ ህግ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ከ"የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ ጾታዊ/ወሲባዊ ትምህርት ክፍል" መርጠው እንዲወጡ ይፈቅዳል፤ ነገር ግን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ ከመሳሰለው ስርአተ ትምህርት አይደለም።

**ስለ አካታች ጽሑፎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡- ፀረአድሎአዊነት፣ እኩልነት እና የባህል ብቃት በሚመለከት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ እና MCPS LGBTQ+ ድረገጽ ይመልከቱ።**

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# ዘወትር የሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs)

| ጥያቄዎች/sQuestions | መልሶች |
|---|---|
| በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት LGBTQ+ ሥርዓተ ትምህርት አለ? | በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት LGBTQ+ ሥርዓተ ትምህርት የለም። |
| ወላጆች መርጠው መውጣት እና አማራጭ ጽሑፍ/ሌላ ሥራ እንዲሰጥ ሊጠይቁ ይችላሉ? | ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በሜሪላንድ ህግ መሰረት በስቴት ከተደነገገው የጤና ስርአተ ትምህርት የተወሰኑ ክፍሎች በስተቀር በማናቸውም ሌሎች የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ከመሳተፍ መርጠው መውጣት አይችሉም። |
| ሁሉም አስተማሪዎች LGBTQ+ አካታች ጽሑፎችን እና ግብዓቶችን መጠቀም አለባቸው? | አዎ፣ አስተማሪዎች ከተለዩ የሊተርሲ ትምህርቶች ውስጥ የተለያዩ አካታች ጽሑፎችን መምረጥ ይችላሉ። |
| ርእሰ መምህራን እና አስተማሪዎች LGBTQ+ አካታች ጽሑፎችን ለተማሪዎች ከስተዋወቃቸው በፊት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል? መፅሃፍቱ ከመነበባቸው በፊት አስተማሪዎች ደብዳቤ ወደ ቤት መላክ ይጠበቅባቸዋል? | የተለያየ ስብጥር ያላቸውን ማስተማር ፖሊሲያችን በመሆኑ፣ የማህበረሰባችንን ብዝሃነት የሚወክል ገጸ ባህሪ ባስተዋወቅን ቁጥር የስርዓተ ትምህርት መርጃዎችን ወይም ጽሑፎችን ለወላጆች ማሳወቅ አይቻልም። |
| ተማሪዎች በክፍል ውስጥ LGBTQ+ አካታች ጽሑፎች ሲማሩ ልጄን እቤት ማቆየት እችላለሁ? | በትምህርት ላይ ስለመገኘት የሚጠበቁ ነገሮች እና መስፈርቶች MCPS ደንብ ላይ ተዘርዝረዋል፦ JEA-RA መገኘት |
| በትምህርት ቤት ስለ ጾታ ማንነት እና ስለ ጾታዊ/ወሲባዊነት ለምንድን ነው ልጄ መማር ያለበ(ባ)ት? | በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥርዓተ-ፆታ ማንነት እና የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይዘት ያለው ማስተማሪያ የለም። መጽሃፎቹ የተለያየ የሰዎችን ስብጥር ያካትታሉ። አካታች መጽሃፎች የተማሪዎችን የመረዳዳት፣ የመተሳሰብ እና ከተለያዩ እኩዮች ጋር የመተባበር ችሎታን ይደግፋሉ፣ እና ለሁሉም ሰው አክብሮት መስጠትን ያበረታታሉ። |
| ልጄ ስለ ጾታ እና ጾታዊ ማንነት ለመማር ገና ትንሽ አይደለ(ች)ም? | በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በጾታ እና በጾታዊ ማንነት ላይ ግልጽ የሆነ መመሪያ የለም፤ ወጣቶች ለተለያዩ የሰዎች ስብጥር ያላቸውን ስሜት እንዲያዳብሩ እና ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ተዛማጅ የሆኑ ማንነቶች መኖራቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። |
| በልጄ አእምሮ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት እሳቤዎች በቤት ውስጥ ከምንከተላቸው እሴቶች ጋር ይቃረናሉ። ልጄ እነዚህን እሴቶች ውድቅ እንዲያደርግ/እንድታደርግ ለማስተማር እየሞከራችሁ ነው? | ተማሪዎች በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የተዘረዘሩትን የስርአተ ትምህርት አመላካች ትምህርት ይማራሉ። ለምሳሌ፦ "የአንድን ታሪክ ድራማ ወይም ግጥም ጭብጥ ከጽሁፉ ዝርዝር ውስጥ ማጤን፣ የጽሑፉን ማጠቃለያ መስጠት።" |
| መጽሐፎቹ እንዴት ተመረጡ? | በዚህ ሂደት ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ MCPS ድረ ገጽ ግምገማ እና ምርጫ ይጎብኙ። |

**ተጨማሪ መረጃዎች፦**
MSDE (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ) የጤና ትምህርት መመሪያ ከቅድመ መዋለ ህጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት